

# አንድነት በክርስቶስ ውስጥ


“ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት
በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።”(1 ቆሮንቶስ 1፡10)

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሰላምታ ከሰጠና ስለ መፈሳዊ እድገታቸው ካመሰገናቸው በኋላ በቤተክርስቲያን ከነበሩ ችግሮች ቀዳሚ የሆነውን የአንድነት አለመኖር ችግርን በተመለከት ይመክራል።

ይህ ችግር በዘመናችን ቤተክርስቲያኖችም ውስጥ ያለ ሲሆን የቆሮንቶስ ሰዎችን መልዕክት ጨምሮ ጳውሎስ በፃፋቸው ሌሎችም መልዕክቶች ውስጥ ይህንን ችግር መፍታት የምንችልበትን መንገዶች እናገኛለን።

ገና ከጅምሩ ግልጽ የሆነው ነገር አንድነት በሰው ጥረት ሊገኝ እንደማይችል ነው። አንድነታችን ሊጸና የሚችለው ኢየሱስ ላይ በማተኮር ብቻ ነው።





- መከፋፈልን የሚያስከትሉ ችግሮች:
  - መከፋፈል እና ክርክር
- አንድነትን መጠበቅ:
  - አንድነት በኢየሱስ
  - ጥበብ እና ብስለት
  - አገልጋይነት እና ራስን ዝቅ ማድረግ
  - መሪዎችን ማክበር

# መከፋፈልን የሚያስከትሉ ችግሮች

# መከፋፈል እና ክርክር

“ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።”
(1 ቆሮንቶስ 1:10)



በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ምን አይነት መከፋፈሎች ነበሩ (1ቆሮ 1:12)?

እንደ ጳውሎስ፣ አጵሎስና ጴጥሮስ ያሉ በርካታ መሪዎች በቆሮንቶስ አልፈው ነበርና እያንዳንዱ ምዕመን ለራሱ የሚመቸውን ሰባኪ መርጦ ነበር። ይህ ጉዳይ አለመስማማትን እስኪፈጥር ድረስ ጎልቶ ነበር (1ቆሮ 1:11)።



የቆሮንቶስ ሰዎች የሁሉም ስብከት አንድ መሆኑን ዘንግተው በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ሲባክኑ ነበር (1 ቆሮ 3:5-8)።

ቀስ በቀስ የቤተክርስቲያን ኑሮ መጎዳት ጀምሮ ነበር (1 ቆሮ 3:3)። አንድነታቸው እጅግ ደቅቆ የጌታ እራት ስነ ስርዓት እንኳን ተስተጓጉሎ ነበር (1 ቆሮ 11:33)፤ በፍርድ ቤትም እስከመካሰስ ድረስ ተቀያይመው ነበር (1 ቆሮ 6:1)።





# አንድነትን መጠበቅ

# አንድነት በኢየሱስ

**"ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።" (1 ቆሮንቶስ 1:9)**

"ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?" (1 ቆሮ 1:13)። ጳውሎስ እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቁ ወደ ልባቸው ይመለሱ ዘንድ ነው።

አንድነት ሊገኝ የሚችለው ኢየሱስን ጌታ በማድረግ ብቻ ነው። አንድነት የሚመጣው ከወንድሞች ወይም ከእህቶች ሀሳብ ጋር ስለተስማማን ወይም የሚቀርቡንን ሰብስበን ስላደምን አይደለም።

በኢየሱስ ያለ አንድነትና ፍጹም የሀሳብ ስምምነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በሁሉም ጉዳይ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ይኖረናል ማለት አንችልም፤ ወይም በተግባራችን ወጥነት ይኖረናል ማለትም አንችልም።

ትናንሽ የአመለካከት ልዩነቶችና የእያንዳንዱ ሰው የተለያየ ተሰጥዖ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሲሆን አለመስማማትን ከመፍጠር ይልቅ አንድነትን ያጎለብታል (1 ቆሮ 12:12-13፣ 25፣ 27)።

በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድነት የሚመጣው እኔነትን በመግደልና ለኢየሱስ በመኖር ብቻ ነው።



# ጥበብ እና ብስለት

"እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም።" (1 ቆሮንቶስ 3:1)

ጳውሎስ ያልበሰሉ ክርስቲያኖችን "በክርስቶስ ሕፃናት" እና "ሥጋዊ" ብሎ ይጠራቸዋል (1 ቆሮ 3:1)። እንዲህ ያሉ ክርስቲያኖች ትኩረታቸው በኢየሱስ ላይ ሳይሆን በሰዎች ላይ ነው።

ለአንዳንድ መሪዎች ከሌሎች ይልቅ ያልተገባ ክብር ሲሰጥ ቤተክርስቲያንን የሚከፋፍሉ ቡድኖች ይፈጠራሉ። ይህ ያለመብሰል ውጤት ነው።
ስለዚህ ጳውሎስ በክርስቶስ ወደ ብስለት እንድንደርስ ይጠራናል (1 ቆሮ 2:6)።

| | አለመብሰል | | ብስለት |
|---|---|---|---|
|  | እንደ ሕፃናት ናቸው (1 ቆሮ 3:1) |  | አዋቂዎች ናቸው (1 ቆሮ 14:20) |
|  | ወተት ብቻ ይጠጣሉ (1 ቆሮ 3:2) |  | ጠንካራ ምግብ ይመገባሉ (ዕብ 5:14) |
|  | ሥጋዊ ናቸው (1ቆሮ 3:3) |  | መንፈሳውያን ናቸው (1 ቆሮ 2:13) |
|  | በሌሎች አመለካከት በቀላሉ ይታለላሉ (1 ቆሮ 3:4) |  | በመንፈስ ይመረምራሉ (1 ቆሮ 2:14) |

# አገልጋይነት እና ራስን ዝቅ ማድረግ

**“እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቍጠረን።” (1 ቆሮንቶስ 4:1)**

ልክ እንደ አሁኑ ዘመን በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ሰዎችም በፖለቲካ፣ በፍልስፍና፣ በኃይማኖትና በሌሎችም አመለካከቶች የተከፋፈሉ ነበሩ። ይህ አይነቱ አኗኗር በቤተክርስቲያን እንዳይዘልቅና መከፋፈልን እንዳያመጣ መከላከል የምንችለው እንዴት ነው?





ለዚህ የመሪዎች አመለካከት ትልቅ ሚናን ይጫወታል። የቤተክርስቲያን መሪዎች የመጋቢነት ሚናቸውን በግልጽ መረዳት አለባቸው። የቤተክርስቲያን ባለቤቶች ሳይሆኑ ቤተክርስቲያንን ለክርስቶስ የሚንከባከቡ ናቸው።



የቤተክርስቲያን መሪዋ ኢየሱስ ነው፤ መሪዎች የሚመሩት “እንደ ክርስቶስ ሎሌዎች” በመሆን ነው (1 ቆሮ 4:1)።

የሚያስተዳድረው አገልጋይ ጌታ እንደሆነው መሆን አለበት፤ ሌሎችን ለማገልገል በትህትና ራሱን ለመስጠት ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን አለበት (ፊል 2:3-8)።



መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ምዕመን እንዲህ ቢሆን ኖሮ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት ያለ አንድነት ይኖር ነበር?

# መሪዎችን ማክበር

“እንደዚህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል።” (1 ቆሮንቶስ 4፡2)




በመሪዎች ዙሪያ የከበበው ሽኩቻና አድመኝነት እንድንተዋቸው ሊያደርገን አይገባም። ጳውሎስ ከዚህ በተቃራኒ በቆሮንቶስ የነበረውን የአጵሎስን አገልግሎትና ስራ ሲደግፍና ሲከክላከል እንመለከታለን (1 ቆሮ 3:5-6፣ 4:6፣ 16:12)።



መሪዎች በታማኝነት ሲሄዱ ክብር የተገባቸው ናቸው (1ቆሮ 4:2፣ 1ጢሞ 5:17)። ነገር ግን ያንን ክብር ባይቀበሉ እንኳን የሚፈርድላቸው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር እራሱ መሆኑን በማወቅ ታማኝ ሆነው መቆየት አለባቸው (1ቆሮ 4:3-4)።



ፍራንክ እና ዋልተር ቦንድ ወደ ስፔን የሄዱ የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን ናቸው። ዋልተር ለእምነቱ ሲል በጃኤን በ1914 ዓ.ም ሞተ።

ክርስቲያን መሪዎች የኢየሱስን ዱካ ተከትለው ለወንድምና እህቶቻቸው ሲሉ መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፤ ካስፈለገም ለአገልግሎታቸው ሞትን እንኳን መጋፈጥ አለባቸው (1ቆሮ 4:11-13; 2 ቆሮ 11:23-28)።



የመሪዎችም ሆነ የምዕመናን ጥሪ እርስ በርሳቸው እንዲጣሉና እንዲከራከሩ ሳይሆን ኢየሱስን ለማክበርና የመስቀሉን ስብከት ለመስበክ እንዲተባበሩ ነው።

“እንደ ክርስቶስ ትዕግስት ያለ በቤተክርስቲያን ውስጥ ፍፁም አንድነትን ሊያጸና የሚችል ምንም ነገር የለም። ሰይጣን አለመስማማትን ሊዘራ ይችላል፤ ክርስቶስ ብቻ ግን አለመስማማቶቹን ሊያጠራ ይችላል.... እናንተ እንደ ግል የቤተክርስቲያን ሰራተኞች እግዚአብሔር በኃይል ስትወድዱትና ባልንጀራችሁን እንደራሳችሁ ስትወድዱ በአንድነት ውስጥ የግድ ጥረት ሳይኖር በክርስቶስ አንድነት ይኖራል፣ የሚያሳብቁ ጆሮዎች ይዘጋሉ፣ ማንም ደግሞ በባልንጀራው ላይ ቅሬታን አያነሳምም። የቤተክርስቲያን አባላት ፍቅርንና አንድነትን ይወድዳሉ፤ አንድ ትልቅ ቤተሰብም ይሆናሉ። እግዚአብሔርም ልጁን ወደ ዓለም እንደላከው በዓለም ፊት እውቅናን በመስጠት ምስክሮች እንሆናለን።”

EGW (Reflecting Christ July 5)